# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"... እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ፡፡" (ኢሳ 48 ÷ 17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Phone 816 – 352 – 6015

**መስከረም** 1996 Sept. 2003 "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል፡፡" (ኢሳ 54÷13)
አዘጋጅ መላኩ ማሞ ትዕዛዙ

www.ethioGodslove.org

"ስለዚህ÷ወንድሞች ሆይ÷መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፡ እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉምና፡ እንዲሁ ወደ ዘላለሙ ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት መግባት በሙላት ይሰጣችኋልና፡፡"
(1ኛ ጴጥሮስ 1÷10-11)

## የሕይወት ተልዕኮ

ተምረው÷ተምረው÷ ካበቁ በኋላ ሰላምና የመንፈስ ርካታ የማያገኙ ሰዎች አጋጥመዋችሁ ያውቃሉ? ነግደው አትርፈው÷ ወይም ተሹመው ከብረው÷ አሁንም ርካታ የማያገኙ ሰዎች አይታችሁ አታውቁም?

ይህ የሚሆንበት ምክንያት እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር የሕይወት ተልዕኮ የመደበለት ስለ ሆነና ነፍስ ሁሉ ያንን ተልዕኮዋን ለመፈጸም ስለምትቃትት ነው፡፡

የሕይወትን ተልዕኮ÷ክርስቲያኖች "ጥሪ" calling ዓለማውያን ደግሞ "የሚያስደስተኝ" passion ይሉታል፡፡ ሁሉም ግን በተለያየ ቋንቋ የሚሉት፡- የተፈጥሮ ስጦታዬንና ትምሕርቴን በሥራ ላይ በማዋል ርካታ የማገኝበት ሥራ ባገኝ ማለታቸው ነው፡፡ ክርስቲያኖች ከአገልግሎት ወደ አገልግሎት÷ ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን÷ በመቀያየር ይህንን ለመፈለግ ይሞክራሉ፡፡ ሌሎቹም፡ ከሥራ ወደ ሌላ ሥራ÷ከከተማ ወደ ሌላ ከተማ በመቀያየር ይጥራሉ፡፡ ትዳርን እንኳን እስከ ማፍረስ የሚደርሱ ታይተዋል፡፡ ይህ ግን መፍትሔ አይሆንም፡፡

በሚከተለው የሕይወትን ተልዕኮ ለማግኘት ሊረዱ የሚችሉትን መሠረታዊ ሃሳቦችን እናቀርባለን፡፡ የሰው ሁሉ የሕይወት ተልዕኮ እንደ ሰዎች ቁጥር ልዩ ልዩ መሆኑን በማሰተዋል÷ እያንዳንዱ ሰው ለየራሱ የአምላኩን ፈቃድ ለሕይወቱ መፈለግ አለበት፡፡ ወንጌል ለመስበክ የተጠራ ሰው÷ በእምቢተኝነት ነጋዴ ወይም ገበሬ ለመሆን ቢሞክር፡- ዘመኑ ሁሉ የተሰናከለና ርካታ የሌለው ይሆናል፡፡ ነጋዴውም ነግዶ በሐብቱ እግዚአብሔርን እንደ ማገልገል ፈንታ÷ ካሕን ካልሆንሁ ቢል ለራሱ መከራን ለሕዝቡም ሁከትን ያተርፋል፡፡

## የሕይወትን ተልዕኮ ማወቅ

1. **የራስን ተፈጥሮና ባሕሪይ መረዳት፡-** ራስን በሚገባ መርምሮ መረዳት ከብዙ የማያስፈልጉ ሙከራዎች የሚያድን ጅማሬ ነው፡፡ ይህም የሚደረገው የራስን ዝንባሌ÷ችሎታ÷ፍላጎት÷የዕምነት አቅጣጫና ጸጋ መርምሮ፡- የምርመራውንም ወጤት በሚያዋጣ ተግባራዊነት በማቀናጀት ነው፡፡ከዚያም ተስውሮ የተቀመጠው ዕውነተኛው ማንነታችን ይገለጥልናል፡፡ ራሳችንንም አበክረን በተረዳን መጠን÷እግዚአብሔር በሕይወታችን እንዲሠራ እንመቸዋለን፡፡

2. **የታወቁትን ልዩ ልዩ ተልዕሎዎች (አገልግሎቶችና ሥራዎች) መረዳት፡-**

መቼም ሰው የማያውቀውን አይመርጥምና፡- ራስን ከመረዳት ቀጥሎ የሚያስፈልገው÷ በሚገባ ጠቃሚ የሚኮንበትን <u>የሥራ መስክ</u> (ተልዕኮ) (አገልግሎት) አውቆ መወሰን ነው፡፡ ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሲታሰብ÷መጀመሪያ የሚመጡት ሰባኪነትና ዘማሪነት ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ምክንያቱም ፊት ለፊት ስለ ሆኑና ስለሚታወቁ ነው፡፡ ሆኖም ካውንስለሮች "career exploration" የሚሉት ይህ የዝግጅት ጥናት በሌለን ጸጋ÷ ባልተሰጠን ኃላፊነት ውስጥ ገብተን÷ ተቸግረን ሌሎችንም እንዳናስቸግር ይረዳናል፡፡

3. **ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ወዳጅነት አጥብቆ መጠበቅ፡-**

ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 15 ላይ የተናገረውን እናስታውስ፡፡ ለምሳሌ በቁጥር 5 ላይ ስንመለከት፡- "እኔ የወይን ግንድ ነኝ፡ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡፡ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና፡በእኔ የሚኖር፡እኔም በእርሱ÷እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል፡፡" ይላል፡፡ እዚህ ላይ ጌታ የሚለን፡- ማንኛውም በእርሱ ፊት ዋጋ ያለው ነገር ከሕይወታችን ሊወጣ የሚችለው÷ ከእርሱ ጋር ካለን ወዳጅነት የሚመነጭ ሲሆን ብቻ መሆኑን ነው ይህ ምን ማለት ነው? የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ዋጋ ከፍለን ከእርሱ ጋር ያለንን ወዳጅነት በጥንቃቄ ማሳደግና መጠበቅ አለብን ማለት ነው፡፡ A Testament of Devotion የተባለው መጽሐፍ ደራሲ፡ ቶማስ ኬሊ እንዲህ ሲል የጻፈው ትዝ ይለኛል፡፡ "እጅግ ብዙ ቅን ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚያደርጉትን ሥራ ብዛት ሲያግበሰብሱ÷ጌታ በሕይወታቸው ሊሠራ ሲናገራቸው መስማት ተስኖአቸዋል፡፡" ይላል፡፡

4. **በራስ ላይ ሳይሆን በሌሎች ጥቅም ላይ አተኩሮ መነሣት፡-**

ክርስቲያኖችም ሆንን ሌሎች ወደ ሥራ ስንሰማራ በአብዛኛው የምናተኩረው በራሳችን ብቻ ላይ ነው፡፡ ደመወዜ ምን ያክላል? ምን ማዕረግ ይጠብቀኛል ምን ክብር አገኛለሁ? የሚሉት ጥያቄዎች የብዙዎች መነሻዎች ናቸው፡፡ እነዚህ አስፈላጊ የሚሆኑበት ሁኔታ ሊኖር ቢችልም፡- ዘላቂ ስኬት የሚፈልግ ሰው በራሱ ጥቅም ላይ ማተኮር የለበትም፡፡ የሕይወትህ ተልዕኮ እንዲሳካልህ፡- <u>"ባለሁበት ቦታና ሁኔታ ለብዙዎች ጥቅምና ለጌታ ክብር÷እጅግ ተፈላጊው ተግባር ምንድን ነው?</u>" <u>ብለህ በመጠየቅ ያንን ፍላጎት ለማሟላት ጸልየህ መነሣት አለብህ</u>፡፡ እግዚአብሔር እጁ÷አፉ÷ ወዘተ እንድሆንለት የሚፈልገኝ÷የት ላይ ነው ብለህ መነሣት አለብህ፡፡ ይህም የስኬት ዋስትና ያለው አጀማመር ለመሆኑ የብዙ አገልጋዮች ታሪክ ይመሰክራል፡፡

ቃሉም፡ "የተለያዩትን የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታዎች በታማኝነት በማስተዳደር ከእናንተ እያንዳንዱ በተሰጠው የጸጋ ስጦታ <u>ሌላውን ያገልግል፡፡</u>"ይላል፡፡
(1ኛ ጴጥሮስ 4 ÷ 10)

አያችሁ? ከእግዚአብሔር ሳይቀበል መልካም የሚያደርግ የለም፡፡ በዘመን ሁሉ በምድር ላይ መልካም ያደረጉ ሰዎች ሁሉም ችሎታቸውን ያገኙት ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ስጦታዎችም ለሰው የሚሰጡት ለደመወዝ መሰብሰቢያ ብቻ÷ለዝና ወይም ለራሳችን ክብር ብቻ አይደለም፡፡ሰዎችን በመጥቀም እግዚአብሔርን ለማስከበር ነው፡፡

ስለዚህ የሰው ተልዕኮ መንፈሳዊ ነው፡፡ እንደ ዕውነቱ ከሆነ÷ጌታን የማያመልኩትም ሳይቀሩ፡- የሰው ሁሉ ተልዕኮ መንፈሳዊ ነው፡፡እግዚአብሔርን ወይም ሴይጣንን÷በአንድ ጊዜ ከሁለቱ አንዱን ነው የምናገለግለው፡፡

በምታደርገው ነገር ሰላምና ደስታ አለህ? በአገልግሎትህ (በሥራህ)ችግር ቢኖርብህም ሰላምና ርካታ ግን አለህ?

ከሌለህ ሕይወትህ በተልዕኮው መስመር ላይ ላይሆን ይችላል፡፡ እንዲህም ከሆነ ከላይ ያቀረብነውና÷ ከታወቁት ክርስቲያን ካውንስለሮች (ኬቨንና ኬይ ብሬንፍሌክ) ከጻፉት የተረጎምነው መልዕክት እንደሚረዳህ እናምናለን፡፡ ጌታ ዓላማውን በሕይወትህ ያከናውን፡ ይሳካልህም፡፡ አንቺም፡፡ አሜን፡፡

## ትዳር

"እናትህ የሸወደችኝን ልንገርህ?" አለኝ አባቴ÷ የሚቻለውን ያህል አፉን ከፍቶ እየሳቀ፡፡ "እስከተጋባንበት ጊዜ ድረስ ዕውነተኛ ማንነቷን አልገለጠችልኝም፡፡አንድ ቀን ፒክኒክ እንድንሄድ ስጠይቃት÷ያለችኝን ታውቃለህ?" አሁንም እየሳቀ÷ድምጹን እስከ መጨረሻው ከፍ አደረገና፡- "ምን? ፒክኒክ ከአንተ ጋር ሄጄ፡ በዚያ ነፍሳት በሞላበት ሳር ላይ ልቀመጥን?" አለችኝ' በማለት በድሮ ግጭታቸው ቀለደ፡፡ እናቴም ስለ አባቴ በጣም የሚገርማት ብዙ ነገሮች ነበራት፡፡ አባቴ ለ(ሐኒሙናቸው) በሞቶር ቢስክሌት ተፈናጥጠው ውጭ ሐገር ለመሄድ መጠየቁ እስከ ዛሬ ድረስ ያንገሸግሻታል፡፡

እኔ ራሴ ከማግባቴ በፊት÷ከዓመታት በኋላ ስለ ትዳሬ ለልጆቼ ምን ታሪክ እንደምነግር አስብ ነበር፡፡ከባለቤቴ ጋር እንዴት ቀስ በቀስ እየተዋሐድን እንደ ሄድን አስቂኝ ታሪክ ለልጆቼ መንገር ምኞቴ ነበረ፡፡ ነገር ግን አባቴ ያወራልኝ የነበረውን ጉድ ማስተዋል የጀመርሁት ከባለቤቴ ጋር ተጋብተን ብዙም ሳንቆይ ነበር፡፡

ከባለቤቴ ጋር ስንጋባ በትዳር ውስጥ አልፎ አልፎ መጠነኛ አለመግባባት እንደሚኖር አውቅ ነበር እንጂ÷ከዚያ አልፎ÷ ተዋድደው በተጋቡ ሰዎች መሐከል የከፋ ጥል ይከሰታል ብዬ አላሰብሁም፡፡ 'ትዳር ችግር የሚሆነው ለአስቸጋሪ ሰዎች ብቻ ነው' ብዬ አስብ ስለነበርሁ ነው፡፡

እንደተጋባን÷ከባለቤቴ ጋር በጣም ተግባባን፡፡ እኔም በጣም ስለምወዳት ሁሉም ነገር በዚሁ መልክ ይቀጥላል ብዬ አስብ ነበር፡፡ ማታ ማታ አብረን መጽሐፍ በማንበብ ሆነ ቲቪ በማየት በደስታ እናመሽ ነበር፡፡



# ወደ እኔ ኑ

እኔም አሳርፋ ችኋለሁ:

## “እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳ ርፋችኋለሁ።”(የማቴ ወ/ 11፥28)

(እአአ በጥቅምት ወር 2001 መልዕክታችን ላይ ያወጣነውን ግጥም ደግመን አሁን ለሰፋው አንባቢአችን አቅርበናል።)

************

የኑሮ ክብደቱ እያንገዳገደ
ዘመንህ ሳይረባህ ፈጥኖ እየነጎደ
ከኋላህ የመጣው ቀድሞህ እየሄደ
የጀመርኸው አንዱም ያልተገባደደ፤

እጅህን ስጠኝና እደግፍሃለሁ
ባሕሩ አያስጥምህ አሻግርሃለሁ
አንዳትነዋወጥ በወጀቡ መሐል
ማዕበሉን አዛለሁ ቃሌ ይደርስልሃል።
ሠራዊት ቢያሳድድህ ማምለጫም ባይታይ
አሳልፍሃለሁ በባሕሩ ክፋይ
ሞገደኛም ሆነህ መንገድህ ቢረዝም
እታገስሃለሁ ፈጽሞ አልጥልህም።

ልብህ አይታወክ በእግዚአብሔር ዕመን
በእኔም ደግሞ ዕመን ነኝ የማስተማምን
ወዳጄ ትሆን ዘንድ ነፍሴን ሰጥቼአለሁ
ፍቅሬ እስከ ሞት ነው መስቀል ላይ ውየአለሁ
መከራህ አይዋጥህ እኔ አስጥልሃለሁ
እጅህን ስጠኝና እደግፍሃሁ።

ተራራ ሸለቆ ባለህበት ቦታ
ሊዋጉህ ቢመጡ ቀድሜ የምመታ
ጊዜ ወይ ሁኔታ ርቀት አይወስነኝ
ጉዳትህን የማልወድድ ጌታም ወዳጅም ነኝ
ወዳጆች ባይጸኑ ጊዜውን እያዩ
ሥጋ ወላጆችም ጥለውህ ቢለዩ
እኔ ግን ሳልጥልህ በስሜ ምዬአለሁ
እጅህን ስጥኝና አሳርፍሃለሁ።

የሕይወት ቃል ኪዳን ከአንተ ጋር ገብቼ
በተጠራህበት ጉዳይህ መጥቼ
በምክር በተግሳጽ ኰትኩቼ አሳድጌ
መንፈሴን ለማሕተም በልብህ አድርጌ
በቃሌ ተሞልተህ ብርሃኔንም ለብሰህ
እንድታበራልኝ ምስክሬ ሆነህ
ተዳክመህ አይቼህ አዝኜልሃለሁ
እጅህን ስጠኝና አሳርፍሃለሁ።

አይከብድህምና ቀሊል ነው ቀንበሬ
በልቤም ትሑት ነኝ ይበጅሃል ምክሬ
ወደ ትምሕርቶቼ ልብህን አዘንብል
ቀንበሬንም አንሣ ሸክምህ እንዲቃለል
ጫናው ያጎበጠህ የዲያብሎስ ጭካኔ
አሳርፍሃለሁ ተጠጋ ወደ እኔ

ዓይኔ በዓለም ሲዞር አንተን አይቼአለሁ
ብቻህን በሞት ደጅ ተመልክቼሃለሁ
ወደ እኔ ኑ እያልሁ ዛሬም እጣራለሁ
መክፈቻው በእጄ ነው ና አሳርፍሃለሁ።
ግጥም በመላኩ ትዕዛዙ

************

**ትዳር...** ወደ ከተማ አብሮ መወጣት፥ ሁሌ ሳቅና ጨዋታ፥ጓደኞቻችንን ጠርተን አብረን መቁረስና መደሰት ነበር። ይህ ሁኔታ ይቀየራል ብዬ የማስብበት ምክንያት አልነበረኝም።

ከማግባቴ በፊት በየሳምንቱ አዲስ መጽሐፍ ማንበብ ልማዴ ስለነበረ፥የሥራጋችን ግርግር እንዳለፈ የማንበብ ልማዴን ቀጠልሁ። ባለቤቴ አንድ ነገር ስትጠይቀኝ፥ መጽሐፉ ከሳበኝ ምንም መልስ አልሰጣትም ነበር። ትንሽ እንጫወት፥ ወይም ሱቅ አብረን እንድረስ ብትለኝ መጽሐፌን ማንበብ ማቋረጥ ስለሚሆንብኝ፥ልብ አልላትም ነበር። እንዲያውም ማቋረጧ ያስመርረኛል። ሳታቋርጠኝ አንድ ገጽ እንኳ ማንበብ እንዳልቻልሁ ይሰማኝ ነበር። የሚያሳዝነው ነገር፥ ባለቤቴ ከትዳራችን የጠበቀችው ከዚህ የተለየ ነበር።

ነገሩ ካለፈ በኋላ ስትነግረኝ፡- “እኔ ያገባሁህ አብረኸኝ እንድትሆን ነበር ፤ አንተ ግን ደባል ሆንኸልኝ” ነበር ያለችኝ። እኔ ግን የታየኝ፡- ከተጋባን ወዲህ ከምን ጊዜውም ይበልጥ አብረን መሆናችን ነው። በዕጮኝነታችን ወቅት አዘውትረን አንተያይም ነበር። አሁን ግን ጧትም ማታም አብረን ነን ብዬ ነው።

“ነፍሴ በብቸኝነት ተጨነቀች” አለችኝ ነገሩ ካለፈ በኋላ ስትነግረኝ። ወላጆቿ በቅርብ ነበሩ። ጓደኞችም ነበሯት።ሆኖም ባለቤቴ፥እኔ ሳላውቅ፥ በብቸኝነት ስሜት ትጨነቅ ነበር። ሠርጋችን ካለፈ ብዙም ሳይቆይ የሆነ ችግር እንዳለ ይታወቀኝ ነበር። ሆኖም ችግሩ እያደር ራሱ ይወገዳል ብዬ ነበር ችላ ያልሁት።

ባለቤቴ ከንባቤ ላይ ስትጠራኝ ብዙ ጊዜ መዝጋቴ ትዝ ይለኛል። ከሚገባት በላይ ጊዜዬን የምትሻማ ይመስለኝ ነበር፡ ይህ ሁኔታ እየተጠራቀመ ሄዶ አንድ ቀን ፈነዳና ጠብ ጀመርን። ትንሽ ከተጯጯኽን በኋላ ባለቤቴ ከእኔ ጋር ሳለማደር ብርድ ልብሷን አንሥታ ሳሎን ለማደር ሄደች። ተከታትዬ ብዙ ከተለማመጥሁና ይቅርታ ከጠየቅሁ በኋላ ታረቅንና ዕውነቴን ልነግራት ወሰንሁ። “በዕውነቱ፡- እኔነቴን ልታስተዪኝ ነው የምትሞክሪው፤ አልሁዋት። እርስዋም ብልጭ አለባትና በሩን በርግዳ ወጣች።

እጅግ አዘንሁ። እንዲያውም በማግባቴ ታላቅ ስሕተት አድርጌ ይሆን ብዬ አሰብሁ። ደግሞም “ጥሩ ባል አይደለሁም ይሆናል” አልሁ። ሆኖም ግን ባለቤቴ ስሜታዊና ከሚገባት በላይ ከባልዋ የምትጠባበቅ ናት እያልሁ ራሴን አጽናና ነበር።

በሚቀጥለው ምሽት ሌሊቱን በሙሉ ስንነጋገር አነጋን ማለት ይቻላል። ሆኖም በመጨረሻ ላይ ችግራችን የቱ ላይ እንደ ሆነ አገኘነው። አባቴ ስለ እናቴ ይነግረኝ የነበረውን ራሴ ደረስሁበት። ፒክኒክ እንሂድ ሲላት የተቆጣችው ትዝ አለኝ። እኔ ከትዳር የምጠባበቀውና፥ባለቤቴ የምትጠባበቀው በፍጹም ለየቅል በመሆኑ ነው።

አልተረዳኋትም እንጂ፥ለሚስቴ ትዳር ማለት፡-ማታ ማታ ቁጭ ብሎ መነጋገር፥ ስለ ሁሉም ማወራት፥ አብሮ መሳቅና መጫወት ነው።

ኖርማን ራይት የተባለ የትዳር አማካሪ ሲናገር “ሰዎች ሲጋቡ፥ እያንዳዳቸው የየራሳቸውን ድብቅ አጀንዳ ይዘው ይቀርባሉ።... ይህም ድብቅ አጀንዳ አስጨናቂ መልኩን መግለጥ የሚጀምረው ከተጋቡ በኋላ ትንሽ ቆይቶ ነው።” ብሎአል።

እኛም የሁሉ ሰው ትዳር እንደ እኛው በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ማለፍ እንዳለበት እየተረዳን ሄድን።እያንዳንዱ ስለ ትዳር ከቤቱ ያመጣውን ልዩ አጀንዳ ትቶ እየተዋሐደና እየተስማማ የሚሄደው ቀስ በቀስ መሆኑን ተረዳን። ነገሩ ግን ስናገባ ምን ያህል መለወጥ እንዳለብን የሚነግረን ለምን ታጣ? ያሰኛል። በቤተ ክርስቲያን የትዳር ትምሕርት ሰጥተውን ነበር። በክርስቲያን ደራሲዎች የተጻፉ መጻሕፍትም ገዝተን አንብበን ነበር። በትዳር ከሸመገሉትም ምክር ተቀብለን ነበር። ሆኖም ይህ ሁሉ ጥረት፡አንዴ ቃልኪዳን ከተለዋወጥን በኋላ ለሚከሰተው ዕውነታ ሊያዘጋጀን አልቻለም።ዕውነቱን ለመናገር፥እኔ ባለቤቴን ያገባሁት፥በስሜቴ ላይ ተመሥርቼ ነው። ትዳራችን ግን በስሜቴ መሠረት ሊንቀሳቀስ አልቻለም

ትዳርን በሚመለከት፥ “...እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ።” በማለት (በኤፌሶን 5፥33) መጽሐፍ ያስተምረናል። እንዲሁም “ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ ...” ይላል። (ኤፌሶን 5 ፥ 22) ይህም ትዳርን <u>አንዱ ሌላኛውን ከራሱ የሚያስቀድምበትና የሚያስበልጥበት፡ መስዋዕትነት</u> ያደርገዋል። ሚካኤል ማሶን የተባለ ደራሲ “የትዳር ሚስጢር” በተባለው <u>መጽሐፉ “በክርስትናችንም ሆነ በትዳር ዕውነተኛው የራስ ጥቅም የሚገኘው ራስን በማገልገል ሳይሆን ራስን ለሌሎች አገልግሎት አሳልፎ በመስጠት ነው።”</u>ይልና “<u>*ትዳር የሚሳካው፥በሁለቱም በኩል የራስን ፍላጎት የመሰዋት ፈቃደኛነት ሲኖር ነው*፡ ዕውነተኛ ፍቅር መስዋዕትነትን እንጂ ፉክክርን አይፈልግመና</u>።”ይላል።

እኔና ባለቤቴ በዓመታት ውስጥ ምን እንደሚያግባባንና ምን እንደሚያጋጨን ተነጋገርን።ከንባብ ጊዜዬን ብዙ መሰዋት እንዳለብኝ ተማርሁ።በጋርዮሽ የሚደረጉ ነገሮችን አገኘን። መሸት ሲል እያወጋን አብረን ወጣ ማለት ጀመርን። አብረን ጥሩ ጊዜ ከማሳለፋችን በፊት ንባብ እንዳልጀምር ውሳኔ አደረግሁ። ከዚያም እኔ ንባቤን ስጀምር እርስዋም ሥራዋን ደስ ብሎአት ትሠራለች።

የትዳርን ጣዕም የተረዳሁት መጽሐፌን ቁጭ አድርጌ ባለቤቴን ማስደሰት ከጀመርሁ በኋላ ነው። ሚስቴን በፍቅር መያዝ ስጀምር መስዋዕት የተባለው ነገር ምንም ከባድ እንዳልሆነ አስተዋልሁ። በኋላም መጽሐፍ ከማንበብ ይልቅ ከባለቤቴ ጋር እያወራሁ ወጣ ማለቱ ይበልጥ እንደሚያስደስት ተረዳሁ።ከመጽሐፍ ጋር ተደፍቼ በማሳልፈው ጊዜ ያልፈኝ የነበረው የባለቤቴ ፍቅር ጸጸተኝ።

ወላጆቼ በትዳራቸው የመጀመሪያ ዓመት ብዙ ልምድ ነበራቸው። እኔም አባቴ ስለ ትዳሩ ሲናገር ለምን እንደዚያ እንደሚስቅ አሁን ይገባኛል። አንድን ሰው የምታገባው ስለ ፍቅር መሆኑን አባቴ ያውቃል። እኔም እየተማርሁ ነኝ። ፍቅርንም በክርቶስ ፍቅር ተንከባክቦ ማሳደግ እንደሚቻል ተረድቼአለሁ። ጌታ ይመስገን። *** (ሮብ ሞል ከተባለ አገልጋይ መልዕክት ተተረጎመ) ***

---

www.gods-love-ethiopia.com

**አዲሱ የዌብ አድራሻችን**

www.ethioGodslove.org

**በቀለለዎት ይጠቀሙ**

---

“ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።” (ወደ ሮሜ ሰዎች 10፥9-10)

# ኢየሱስ ጌታ ነው
# ጌታ ይባርክህ

መላኩ፥ ዓለምና ሊበን ትዕዛዙ